# የኛ ትውልድ

**አንፃራዊ ዕይታ፤ ላለንበት አጣብቂኝ የፖለቲካ ሁኔታ**
**ከመፍትሔ ፍለጋ አኳያ፤ ገፀ ባህሪያችንን ለመጠቆምና፤ ውይይት ለመክፈት፤**
***ከይነጋል በላቸው - የካቲት ፳፻ ዓ. ም.***

***አንድን ትውልድ ከዚህ ቀን ጀምሮ እስከዚህ ቀን ድረስ ባለው ወቅት የተወለዱ ብሎ መከለሉ፤ በጣም ከባድ ነው።*** የታሪክ ሂደትና የሰዎች የመረዳት ፍላጎት ደግሞ፤ ይኼንን ማድረግ የግድ ይላል። እናም፤ በዚህ ላይ ተራኪዋ እና ተራኪው በተወለዱበት ወቅት ዙርያ ራሳቸውን ለመመደብ፤ የኅብረተሰቡን የታሪካዊ ጉዞ የማረፊያ ቦታዎች መነሻና መድረሻ አድርገው በመውሰድ፤ የትውልድ ክፍፍሉን ያጠናቅቁታል። የኔም አሸናሸን ከዚሁ ወገን ነው።

እኔ ራሴን የመደብኩበትን ትውልድ ገፀ ባህሪ ከመዘርዘሬ በፊት፤ ከዚሁ ትውልድ ቀደም ያሉትን ሁለት ትውልዶች መጠቆሙ፤ የዚህን የኔዉን ትውልድ ክልልና ገፀ ባህሪ ግልፅ ያደርገዋል ከሚል ዕምነት በመነሣት፤ ለነኚህ ቀደም ላሉት ሁለት ትውልዶች አንፃራዊ ገላጭ ገፀ ባህሪ በመሥጠት እጀምራለሁ። በቅድሚያ የየትውልዱን ደንበር ማካለሉ የግድ ይላል። ከዚህም በፊት የትውልድን ፅንሰ ሃሳብ በመዘርዘር የአንባቢያንን ስምምነት ለመገብየት እሞክራለሁ። ቀጥዬ የየትውልዱን መከሰቻ የታሪክ ወቅት ለማካለል የተጠቀምኩበትን መንገድ አሳያለሁ።

***አንድ ትውልድ በክስተቱ ሊመደብበትና ሊጠየቅበት የሚችል የራሱ የሆነ የታሪክ ወቅት አለው።*** ይህ ወቅት ተመዳቢውና ተጠያቂው ትውልድ፤ ካለፈው እና ከቀደመው ትውልድ ተረክቦ፤ በቀዳሚነት የኅብረተሰቡ አንቀሳቃሽ ኃይል በመሆን፤ ለተኪው ትውልድ ቦታ እንዲለቅ እስከተገፋበት ድረስ ያለው ዘመን ነው። በሕፃንነትና በለጋ ወጣትነት የሚገኙበት ወቅት፤ የማደጊያና የመማሪያ ጊዜ ስለሆነ ተመዳቢውና ተጠያቂው ትውልድ የዘመኑ ባለቤት ሊሆን አይገባውም። ይህ እንግዲህ ከትውልድ እስከ ፳ ዓመት ድረስ ያለውን ያካትታል። በዚህ ከተስማማን፤ የዚህ ትውልድ የኅብረተሰቡ ባለቤትነት፤ የሚቀጥለው ትውልድ ፳ ዓመት እስኪሞላው ድረስ ያለው ክፍል ይሆናል ማለት ነው። ይህ ጊዜ ደግሞ የትውልዱ አባላት ከ፳ እስከ ፵ ዓመት ባለው የዕድሜ ክልላቸው የሚገኙበት ወቅት ነው። ይህ ማለት ከትውልድ እስከ ፳ ዓመት ባሉበት ወቅት ከፊታቸው የቀደማቸው ትውልድ እየኮተኮተ የሚንከባከባቸውና የሚያድጉ የሚማሩበት ጊዜ ሲሆን፤ ከ፵ ዓመት በኋላ ደግሞ፤ መሯሯጡን ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስረክቡበትና የተለዬ ሚና የሚጫወቱበት ወቅት ነው። በቀደማቸውና በሚከተላቸው ትውልድ ዘመን የሚጫወቱት አመዛኝ የሆነ ሚና አላቸው። የዘመን ባለቤትነታቸው ግን በክልላቸው የታጠረ ነው። እዚህ ላይ አንባቢያን ሊረዱልኝ የምመኘው፤ <u>ይህ አከፋፈል፤ ሳይንሳዊ ወይንም የቀደመ የጥናት መሠረትን የተመረኮዘ ሳይሆን፤ ትውልድን ለመግለፅና ለመረዳት ያመቻል ከሚል የግል ግንዛቤዬ በመነሣት ነው።</u> በተጨማሪም የየትውልዶች መደራረብ የግድ የሚኖር ሃቅ ነው። ***አጠቃላይ የዚህ ፅሑፍና ትንታኔዉ፤ እኛ በአንድነት ያከናወንነዉንና ያጎደልነዉን በመጠቆም፤ በአሁኑ ወቅት ላለንበት ቀውጢ ሁኔታ፤ መፍትሔ ከመሥጠት አኳያ፤ በግልና በኀብረት ልናደርግ የምንችለውንና የሚገባንን ለማሣዬት ነው።***

እስከ አሁን በተዘረዘሩት የተወሰነ ስምምነትን ተጋርተን፤ ወደአብዩ የየትውልዱ ወቅት አመዳደብ፤ ፊታችንን እንመልስ። በአንድ በኩል ከ፲፱፻ ዓ. ም. እስከ ፳፻ ዓ. ም. ያለፈውን ምዐተ ዓመት ከአምስት በመክፈል መመደብ ያስኬዳል። በሌላ በኩል ደግሞ፤ የሀገራችንን ታሪካዊ ጉዞ የማረፊያ ቦታዎች፤ መነሻና መድረሻ ብናደርግ፤ ***<u>ከጠላት ወረራ በፊት</u>፤ <u>በጠላት ወረራ ዘመን</u>፤ <u>ከጠላት ወረራ በኋላ</u>፤ <u>ቀጥሎ የመጣው ትርምስ</u>፤***

*እና **የተከተለው ውጥንቅጥ**፣* በአሁን ጊዜ ደግሞ ከ፷፮ ዓ. ም. በኋላ ***ሀገርን የማዳን ተልዕኮ***፤ አይነተኛ አመላካቾች ናቸው። በዚህ እሽታን ከገዛሁ፤ ወደጀመርኩት የቀዳሚ ሁለት ትውልዶች ትንታኔ ፊቴን ላዙር።

*በፋሺስት ጣልያን ወረራ ወቅት፤ የሀገሩን ዱርና በረሃ ምሽጉ አድርጎ፤ አረመኔውን ጠላት መተንፈሻ አሳጥቶ፣ አንድነትን፣ ኢትዮጵያዊ ቆራጥነትን፣ ከግል ሕይወትና ጥቅም ይልቅ ለወገንና ለሀገር መሰዋዕትነትን በልቡ ቋጥሮ፣ ለተከተለው ትውልድ ያስረከበው **የአርበኞች ትውልድ** ነበር።* እዚህ ላይ ስለ አንዲት አርበኛ፣ ወይንም ስለ አንድ ፊታውራሪ፣ ወይንም ስለአንድ የመንደር ጦር አባላት አይደለም የማነሣው። የዚህ ትውልድ አባላት፤ የሀገሪቱን መሀልና ዳር፣ ምሥራቅና ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ፣ በአርበኝነታቸው ያጥለቀለቁ ነበሩ። ይህ ትውልድ ባህሉን፣ ዕምነቱን፣ ወጉንና ማዕረጉን፣ ሀብቱንና ንብረቱን በሙሉ፣ ሀገሩን ለመከላከል የዳረገ ትውልድ ነው። ይህ ትውልድ በአስር ወይንም በመቶ፣ በአንድ ሺህ ወይንም በአንድ መቶ ሺህ የሚቆጠር ሣይሆን፤ በሚዘገንን መንገድ ከዚያ በላይ የሆነ ቁጥር በትግሉ ሰዉቷል። እንግዲህ ይኼንን ያህል ኢትዮጵያዊ ከተሰዋበት፤ በአጠቃላይ ሀገርን በመከላከሉ የታሪክ ግዳጅ ምን ያህሉ ቢሠማራ ነው? በኔ ዕምነት፤ ያለምንም ማመናታት፤ መላው ትውልድና በዚያ በታሪካዊ ክንውኑ አጋጣሚ በወቅቱ የተገኙ ከዚያ በፊትና በኋላ የነበሩ ትውልዶችን አክሎ ነው። እናም ይህ ትውልድ፤ ***አርበኝነት***፤ የባህሪው መግለጫ ይሆናል። ከነኚህ ወርቅዬ ንብረታችን በመከተል የተረከበው ትውልድ፤ ***የግንባታው ትውልድ*** ነው።

***የግንባታው ትውልድ** በፋሽስት ጣልያን የተነጣጠለ ቤተሰቡን ሰባስቦ፣ በውርጅብኝ ቦምብ የጋዬ ባድማውን አቅንቶ፣ ያለቀ ንብረቱን የተበተነ ከብቱን ለቃቅሞ፣ አዲስ ጅምር ሕይወት፣ አዲስ ንብረት፣ የመሠረተ ትውልድ ነው።* ጥቂቶች በንጉሡ ዙርያ የተገኙና ሥርዓቱን እንዲያገለግሉ የታጩ የገዢው ክፍል አባላት ልጆቻቸውን፤ አዲስ ትምህርት፣ ከቄስና ከቁርዓን ትምህርት ቤት ጎን አስኳላ አስገብተው፤ በያለበት ትዳር መሥርተው፤ ታሪካዊ ተልዕኳቸውን አጠናቀዋል። *ይህ **የግንባታ ትውልድ** ለፋሽስቱ ትግል ያልደረሰ፣ ከርሱ በፊት እንዳለፉት ሁሉ ንጉሠ ገሥቱን እንደ ንጉሠ ነገሥቱ ፍላጎት የተቀበለ፣ ሀገሪቱን እንደ ንጉሠ ነገሥቱ የግል ንብረት የወሰደ ነበር።* በዚህ ትውልድ ከራሞ፤ ሁሉ ሰላም፣ ሁሉ ቀና ነበር ማለት አይደለም። ከሽሽት ተመልሰው የመጡት ንጉሥ፤ ከሀገር ግንባታና ወደፊት መምራት ይልቅ፤ ተቃዋሚዎች ይሆኑኛል የሚሏቸውን ማጥፋት፣ የሀገሪቷን መሬትና ንብረት ለቤተሰባቸውና ለአሞጋሾቻቸው መደልደልና፣ ዘለዓለማዊነታቸውን መለኮታዊ ቅብዓ ቅዱስ አስቀብተው፣ ትምህርቱን፣ ፍርዱን፣ ሥነ ሥርዐቱን በሙሉ የዚሁ አገልጋይ ማድረጉን ተካኑት። የዘራሽውን ታጭጃለሽ ሆነና፤ መሬት ከነጢሰኞቹ በሠጧቸውና ውጭ ሀገር ልከው ባስተማሯቸው አገልጋዮቻቸው አማካኝነት፤ ሀገሪቱን ለጥቂት ጊዜ በዚሁ ማነቆ አሰሯት። እነ በላይ ዘለቀን ሰቀሉ። እነደጃች ነጋሽ ወርቅነህንና ደጃች አበረን ለግዞት ዳረጉ። በነገራችን ላይ እነኚህን ለትምሣሌ ጠቀስኩ እንጅ፤ ሀገር ወዳድ አርበኛ በመሆናቸው በእስር የማቀቁና ባንዳ ሆነው ለንጉሡ በመስገዳቸው የተሸለሙ ብዙዎች ናቸው። *ጊዜና የዓለም ግሥጋሤ ኢትዮጵያን ቆሞ የመጠበቅ ግዴታ አልነበረበትምና ጥሎን ሸመጠጠ። በአንፃሩ፤ ዓለም ያለ እኛ፤ እኛ ያለ ዓለም አልኖርንምና፤ በዓለም ዙርያ የሚከናወኑ ክስተቶች፤ የሀገሪቱን ክንንብ ነጠላ ገፍፈው፤ ሀገሪቱ ከቀሪው ዓለም አንፃር የት እንዳለች፤ በጣት ለሚቆጠሩ ጥቂት የዚህ ትውልድ አባላት፤ ግልፅ አደረጉላቸው።* በዚህ ወቅት የተከሰቱትን፤ የ፲፱፻፴፭ ዓ. ም. የወያኔ እንቅስቃሴን፣ የ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. መፈንቅለ መንግሥት ሙከራን፣ የ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. የባሌ መነሣሣትን፣ በጠቅላላው የአርሶ አደሮች በዬቦታው የራሳቸውን ጥያቄ ይዘው መነሳታቸውን፣ እና ሠራተኞች ተደራጅተው ለመብታቸው ለመከራከር መነሳታቸውን፤ ይዘክሯል። እንግዲህ ይህ የዚህ

ትውልድ እንቅስቃሴ የወደስተፊቱን አመልካችና መሠረት ቢሆንም፤ ለዚህ ትውልድ ባህርይ መግለጫ ሆኖ አይቀርብም። እዚህ ላይ መሠመር ያለበት፤ ይህ ትንታኔ፤ የዚህን ትውልድ ጥረት ለማንኳሰስ ሳይሆን፤ ተሣታፊ አባላቱ ከመላ የትውልዱ አባላት አንፃር ቁጥራቸው ሲታይ፤ ወቅታዊ ሚዛናቸውን ያደፋል ወይ ነው? መልሱ ግልፅ ነው። ሚዛናቸውን ሊያደፋ ቀርቶ፤ ምጣዳቸውን አያሰማም። እናም ይህ ትውልድ፤ ግንባታ፤ የባህሪው መግለጫ ይሆናል። ይህ የግንባታ ትውልድ የተገፋው እኔ አባል በሆንኩበት ትውልድ ነው።

የዚህን እኔ አባል የሆንኩበትን ትውልድ መግለጫ ገፀ ባህርይ ከመጠቆሜ በፊት፤ ይህ ትውልድ ሀገሪቱን ከቀደመው ትውልድ በምን ሁኔታ እንደተረከበና በምን ሁኔታ ለቀጣዩ ትውልድ እንደተወ መግለፅ እፈልጋለሁ። እዚህ ላይ ለአንባቢያን የተለመዱ አባባሎችን ላመላክት፤

“ ቀድሞ በኛ ጊዜ . . . . ”
“ የዛሬ ዘመን ልጆች . . . ”
“ እኛ ልጆች ሳለን . . . . ”
“ የወርቁ ዘመን ድሮ አለፈ ”
“ ዛሬ ዛሬማ . . . . . . . ”

እነኚህ አባባሎች፤ ትንሽ ትንሽ ቅያሬዎችን በማካተት፤ ከትውልድ ትውልድ ሲነገሩ የነበሩና ለወደፊትም በትርጉም አንድነት ባለው መልኩ፤ በአባባል ግን ሊቀየር በሚችል መልክ፤ ይቀጥሉ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ። በጥቅሉ እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ትውልድ፤ ከሌሎቹ ሁሉ የላቀ፣ በጥበብ የመጠቀ፣ በዘመናዊነት ወደር የሌለው፣ ሲያዳዳውም ዘለዓለማዊ አድርጎ፤ በኪነ ጥበቡ ማንቆለጳጳሱ፤ በዘፈኑ ማሞገሱ፣ በስዕሉ ማሣመሩ፣ በስነ ፅሑፉ ማድነቁ፣ እና በትያትሩ ማሞካሸቱ፤ አያስደንቅም። የሁሉም ትውልድ ባህሪ ነውና። ይህ እንግዲህ ታሪክ ይኼንን ትውልድ በ“ዛሬ” ክልል በማስቀመጡና ይህ “ዛሬ” ሁሌም በትናትና እና በነገ መካከል የሚኖር በመሆኑ ነው። *ይህ “ዛሬ” ግን ለዚሁ ትውልድ ብቻ እንጅ ዘለዓለማዊ “ዛሬ” አለመሆኑን ትውልዱ የሚገነዘበው፤ የነገው ትውልድ በር አንኳኩቶ የዚህን ትውልድ “ዛሬ” የራሱ “ትናንት” ሲያደርገው ነው።* እኔ አባል በሆንኩበት ትውልድ ያሉ ጥቂት አባላት፤ ትውልዱን ወርቃማው ትውልድ ሲሉ ተስተውለዋል። ሃቁን ግን ልመለስና፤ በ፲፱፻፷ ዓ. ም. ተረክበን በ፲፱፻፹ ዓ. ም. ያስረከብናት ሀገራችንን፤ ምን አከልንላት? ምን አጎደልንባት? በ፲፱፻፷ ዓ. ም. በ፳ ዓመት አካባቢ በዕድሜ ክልል የነበርን እና በ፲፱፻፹ ዓ. ም. በ፵ ዓመት አካባቢ የነበርን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የባህርያችን መግለጫ ምንድር ነው? ምን ዓይነት ጥላ ነው ጥለን ያለፍነው? ሀገሪቱማ እንደኖረችው ኖራለች፤ ለወደፊቱም እንደምትኖረው ትኖራለች። የኛ ሕይወታችን የኑሮ ትምህርት ቤታችን ሣይሆን፤ ኑሯችን ነው። በዚህ በኛ ትውልድ፤ በዚህ በኛ ዘመን፤ ምን ፈየድን? ከመጀመሪያውስ፤ የዚህ ትውልድ አባላት እነማን ነን?

ጥያቄዉ እየበዛ ስለሄደ መልሱን መዳፈሩ፤ የሃሳብ ፍሰቱን ፈር ያስይዘዋል።

አንደኛ የ፲፱፻፷ ዓ. ም. ኢትዮጵያ፤ ከጥቂት የአፍሪካ ሀገሮችና ከአንዳንድ የእስያና የደቡብ አሜሪካ ሀገሮች ሻል ያለ የነፃነት፣ የኢኮኖሚ፣ የትምህርትና፣ የአስተዳደር ይዞታና ቦታ ነበራት። መገንዘብ ያለብን ይህ አባባል አንፃራዊ መሆኑን ነው። በወቅቱ ከነበሩት ያደጉና በመሸጋገር ከነበሩት ሀገሮች አኳያ ኋላ ቀር ነበረች። ይህ እንዳለ ሆኖ፤ በድህነት ከኢትዮጵያ ዝቅ ያሉና በቅኝ ግዛትነት የተቀበሩና የሚማቅቁ የኢትዮጵያን ደረጃ የሚናፍቁ መኖራቸውን ለመጠቆም ነው።

ሁለተኛ የዚህ ትውልድ አባላት በወቅቱ በነበረው አንድ ዩኒቨርሲቲ፤ በለስ በሆነ መንገድ ቀንቷቸው፤ ሁሉም አልተካተቱም። በዕርግጥ፤ ከትውልዱ ከአንድ በመቶ አንድ አሥረኛ ያነሰው ክፍል፤ ይህ ዕድል ገጥሞታል። ከዚህ ኢምንት ቁጥር አሁንም በጣም ጥቂት የሆነው ክፍል ለወገኑ መብት ተዋድቋል። በአንፃሩ ከዚህ ቁጥር እጅግ በዛ ያለው ክፍል ደግሞ የራሱን ጥቅም በማስቀደም በሕዝብ አናት ላይ ጨፍሯል። ተጨባጭ ገፅታ ለመሥጠት፤ *መለሰ ዜናዊ፣ ኢሳያስ አፍወርቂ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ኃይሌ ፊዳ፣ ሰናይ ልኬ፤ ሠይፉ ጠናና እዮብ ጠና፣ አሊ ሙሳና መላኩ ተፈራ፣ ብርሃነ እያሱና ማርታ መብርሃቱ፤* የዚህ ትውልድ አባላት ናቸው። አንባቢ እንክርዳዱን ከእህሉ ለይቶ ማዬት ይችላል። ያም አለ ያ፤ ሁሉም የዚሁ ትውልድ አባል መሆናቸው ግልፅ ነው። እንግዲህ ሠይፉንና እዮብ ጠናን፣ ብርሃነ እያሱንና ማርታ መብርሃቱን የወርቃማው ትውልድ አባል አድርጎ፤ መንግሥቱ ኃይለማርያምን፣ አሊ ሙሳንና መላኩ ተፈራን፣ ከአባልነት ለማስወጣት መሞከር ከታሪክ ሸውራራነት ሌላ የግንዛቤ ዕጥረትን ያመላክታል። ሆነም ቀረም ይህንን የትውልዱን ከአንድ ሺ አንድ የማይሆን ክፍል ለመመልከት ስንል ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኙን ወደጎን ማለቱ አግባብ ስላልሆነ፤ በዚሁ ይገታል። *በንጉሡ ዘመን ኢትዮጵያዊያን አምስት መቶ ብቻ ነን አሉ እንደተባለላቸው፤ የለም እኛ ጥቂቶቹ ነን የትውልዱን ገፀ ባህርይ የምንወስነው ባዮች ካሉ፤ አድማጭ ያክብራችሁ በማለት ልዩነታችን ይሠመርበታል።*

**ሽምግልና መጣ እባላለሁ። በመሽምገል ላይ ያለው ትውልድ አባል ነኝ።** ይኼንን ሠርቻለሁ፤ በዚህ ተካፍያለሁ፤ እያልኩ እራሴን ማኩራራት፤ በግልባጩም ያንን ሣላደርግ ቀረሁ፤ በዚያ ጊዜ ይኼንን ባለማድረጌ እንዲያ ሆነ እያልኩ አንገቴን መድፋት ለመንፈሴ፤ የግሌ ትግል ነው። በኢትዮጵያዊነቴ፤ ታሪክ የመደበልኝን ትውልድ ሳስስ የማገኘው ስሜት ምንድር ነው? ነው ጥያቄዉ። ይህ ትውልድ ከኔ ትንሽ ቀደም ብለው የተወለዱትን እና ከኔ በኋላ ትንሽ ዘግየት እና ዘግዬትየት ብለው የተወለዱትን ያካትታል። ራሴን መካከል ላይ ማስቀመጤ ሣይሆን፤ አካላይ ደንበር አለመሆኔን ለመጠቆም ነው።

እዚህ ላይ በ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. የተከሠቱት የጥላሁን ግዛው በመንገድ ላይ በንጉሡ አገልጋዮች መረሸን፣ የደጃች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ሙከራ፣ በለጋ አዕምሮዬ ላይ ያሣደረው ብልጭታ በወቅቱ የነበረውን የዘውድ አገዛዝ የምመለከትበትን መነፀር ቀይሮታል። ጥላሁን ግዛው ተመትቶ ሲወድቅ ቀድመው ደርሰው ሬሳውን ካነሡት መካከል አንዱ ነበርኩ። በዚያ ሰዓት የቀድሞው የ“ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል” ዶክተር አለመተባበርና መሠወር፣ ወደ ደጃች ባልቻ ሆስፒታል ለመውሰድ ያደረግነው መሯሯጥ፤ እነደ እግሬ እና እነደ እጄ ከኔ ጋር አብሮኝ ይኖራል። በዚያ ቀንና በዚያ ሰሞን የነበርኩበትን ሰመመን፤ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሃንስ፣ ፓትሪስ ሉሙምባ፣ ማልኮለም ኤክስ፣ ኢንድራ ጋንዲ፣ ሳልቫዶር አዬንዴ፣ ኬኔዲ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ እና ቤናዚር ቡቶ፣ የሞቱ ዕለት፤ ደጋፊዎቻቸው የተሰማቸውን ይመስላል ብል ዕውነቱን ጠቅልሎ አያቅፍልኝም። ይልቁንም ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ በአንድነት በአንድ ጊዜ ለአንድ ደጋፊ ግለሰብ ቢፈፀም፤ የሚሰማትን ነበር የሆነብኝ። ይህ የግል ስሜቴ ግን ከትውልዳችን ገፀ ባህሪ አኳያ አስተዋፅዖዉ ቀላል ነው። በዚያ ወቅት በሀገራችን ሠፊ ምድር፤ የጥላሁን ግዛውን ማንነት ቀርቶ፤ መፈጠሩን የማያውቀው የኛ ትውልድ አባላት፤ ቁጥሩ ይበዛ ነበርና።

አሁን የኔው ይብቃና ከእኔ ወደኛው ትውልድ በመመለስ፤ ሀገሪቱን በምን ሁኔታ እንደተውናት እንመልከት። ከ፲፱፻፷ እስከ ፲፱፻፹ ዓ. ም. በነበረው ጊዜ ውስጥ በሀገራችን፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ሞት ትርጉሙ ተቀየረ። ***የትናንቱ ለዛሬው ትውልድ ማስተማር፣ የዛሬው ደግሞ ለነገው ማስረከብ የነበረበት ውስብስብ ታሪካዊ***

***ግዴታ ክሩ ተበጠሰ።*** ከ፲፱፻፷ ዓ. ም. ጀምሮ መተላለፍ የነበረበት ኢትዮጵያዊነት እንደ እሬያ ታጥቦ ጭቃነት መነሣትና መዉደቅ፤ መፅዳትና መጉደፍ፤ ገጠመው። በዬትውልዱ ሀ ብሎ መጀመር ዕጣው ሆነ። “ያለፈው ትውልድ ምንም አያውቅም። ምንም ሊያስተላልፍልን የሚችለው ነገር የለም” ተባለ። አዲስ ኢትዮጵያዊነትን መፍጠር የትውልድ ተልዕኮ ተብሎ ተወሰደ። ደርግ አዲስ ኢትዮጵያዊነትን አወጀ። ህወሀት ደግሞ ሌላ ኢትዮጵያዊነትን አስከተለ። በኢትዮጵያዊነት ላይ የኢትዮጵያዊነት ጎኑ ሳይሆን፤ የተርጓሚው ፍላጎት እግሩን አፈራጦ መሐል ሠፈረበት። ***ኢትዮጵያዊነት ከታሪክ፣ ከባህል፣ ከማንነት፣ መቆራኘቱ ቀርቶ፤ ጥቂት የቡድን መሪዎች እንዳሻቸው የሚጠመዝዙት የፍላጎታቸው፣ የምኞታቸው፣ የስሜታቸው፣ ሰለባ ሆነ።***

ኢትዮጵያዊነት በአንድነት የጋራችን፤ እና ካለፉት ትውልዶች አቆራኝቶ፤ ከወደስተፊት መጪ ትውልዶች ጋር የማስተሳሰር እትብትነቱን አጣ። የአንድ ወቅት ኢትዮጵያዊነት የሌላ ወቅት ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ሆኖ ተፈረደ። እናም ኢትዮጵያዊነት መሠረት የለሽ ተንሣፋፊ ሆነ። ይህ ነው በዚህ በኛ ትውልድ የተከሰተው ዕውነታ። በ፲፱፻፷ ዓ. ም. በጎጃሙ ገበሬ ንቅናቄ የተጀመረው ዘመናችን፣ በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. የተማሪዎች ዉጥረት ተከትሎ፣ በ፲፱፻፷፮ ዓመተ ምህረቱ ፍንዳታ ተናወጠ።

***፲፱፻፷፮ ዓ. ም. በሀገራችን አልባሌው ኢትዮጵያዊ ታሪክ የሠራበት ዓመት ነው።***
በአንፃሩም፤ የኤርትራ ንቅናቄዎች ጎለበቱ። ደርግ የሕዝቡን እንቅስቃሴ በጉልበት ነጠቀ። ኢህአፓና መኢሶን ተፈጠሩ፣ እርስ በርስ ተባሉ። እስር ቤት መታጎር፣ መገደል፣ መገንገላታት፣ መሰደድ፣ የትውልዳችን ዕጣ ሆነ። እዚህ ላይ የአንድ መቶኛ አንድ መቶኛ ስለሆነው ክፍል ሣይሆን፤ በዛ ብሎ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሠተውን ዕውነታ ለማሳዬት ነው። ገፀ ባህርያችንን የሚገልፀው ከቁጥር የሚገባው ክፍል በንቃት የተሣተፈበት ክንውን ነውና። አስከሬን ገንዘብ መሰብሰቢያ ሆነ። የሕፃናት፣ የወጣትና፣ የአዛውንት አስከሬን እንደቁሻሻ ከቤት በራፍ ተጥሎ በከተ። ወንድም በወንድሙ ላይ፣ ልጅ በአባቷና በእናቷ ላይ የደም እጃቸውን አነሱ። ፍርሃት በአደባባይ፣ ፍርሃት በማጀት፣ ፍርሃት ሰው ሲያዩ፣ ፍርሃት ሰው ሳይኖር፣ ፍርሃት በጎረቤት ሰው፣ ፍርሃት በገዛ አባትና እናት፣ ነገሠ። ታትሮ መሥራት፣ ተምሮ ማወቅ፣ ተከባብሮ መኖር፤ ለካድሬና ካድሬነት፣ ለጥቆማና፣ ሰውን ለማስገደል ቦታ ለቀቀ። ሕብረት ጠፋ፣ ድህነት ነገሠ፣ በሽታ በሀገሪቱ ከደመ፣ ድንቁርናም በሀገሪቱ ቤቱን ሠራ። እኔ ይኼንን አላደረግሁም፤ ተፈፀመብኝ እንጅ፤ ብለን በግል ለማምለጥ መሞከር የዋህነት ነው። የትውልድ ገፀ ባህርያችንን የሚናገረው፤ ትተን ያለፍነው የሀገራችን ሁኔታ ነውና! ይህ ደግሞ እኛ አልፈን ስንሄድ፤ በተከተለን ትውልድ ( <u>የውጥንቅጥ ትውልድ</u> ) ላይ የፈጠረውን ግለሰበኝነትና በቀደመው ትውልድም ሆነ በታሪኩ ላይ ለተፈጠረበት ምሪት ቀጥተኛ ኃላፊነታችንን የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል።

***ሀገራችን ላለችበት ቀውስ የኛ ትውልድ አባላት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገናል።***
ይህንን ስል፤ ለምስቅልቅሉ ሁሉ ተጠያቂው፤ ይኼ የኛ ትውልድ ብቻ ነው፤ ማለቴ አይደለም። በተጨማሪም ይህ የሁላችን ጥቅል የገፀ ባህርያችን መግለጫ ሆኖ፤ በግለሰብ ደረጃ ችሏቸው ከፍ ብሎ የሚያበራ አባላት አሉን። ጥላሁን ግዛው አንዱ ተጠቃሽ ሲሆን፤ በከምባታና ሃድያ፣ በባሌ በከፋና በአሩሲ መሬታችን ለኛ ይገባል በማለታቸው በዕስር ማቅቀው ሕይወታቸው ያለፈ ብዙዎች ይገኙበታል። በደርግ የሠራዊቱ አባል በመሆን ከልባቸው “ለሀገሬ ነው የምሠዋው” በማለት በዬጦር ሜዳዉ የወደቁት ወገኖቻችን ቁጥራቸው ከወዲሁ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፤ በሀገር አቀፍ የፓለቲካ ድርጅቶችና በዬ“ነፃ አውጭ” ግንባሮች ተሠልፈው፤ ጭቆናን በመቃወም፣ ፍትህን በመሻት፣ ሕወታቸውን ለወገናቸው አሳልፈው የሰጡትም ቁጥራቸው ከዚሁ

ነው። እዚህ ላይ በጎላ ቀለም ደመቅ ብሎ መሠመር ያለበት፤ ይህ መዝገብ የነኚህ የ"ነፃ አውጭ" ግንባሮች መሪዎችን አለማቀፉን ነው። አጀንዳቸው ከተሰው ቆራጥ ወጣት ተከታዮቻቸው ጋር በምንም መንገድ፤ በማናቸውም ሰዓት አይገጥምምና። አልነበረማ! *በሥልጣን ላይ ቁጥ ያሉትም ሆነ ቋምጠው የቀሩት የትውልድ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ቀርቶ ምን እንደሆነ ማወቃቸው በጥያቄ ይቀመጣል።*

ዝርዝሩን ገታ አድርገን እስኪ ለዚህ ለተተራመሠ ትውልድ ገፀ ባህሪ መግለጫ ይሰጠው። እኮ ሌላ ምን ይባላል! **የትርምስ ትውልድ** እንጅ! ሀገሪቱ የተተራመሰችበት ወቅት ነበር። ኅብረተሰቡ የተመሠረተበት የኅብረተሰብ የልቅና ቋጠሮው የተተራመሰበት ወቅት ነበር። ባህል፣ ወግ፣ ስነስርዓት፣ ዕምነት፣ ክህደት፣ ዕውነት፣ ውሸት፣ መማር፣ አለመማር፣ ሀገር ወዳድነት፣ ሀገር ከሃዲነት፣ መከባበር፣ መካካድ፣ . . . የተተራመሰበት ወቅት ነበር። ብዙ መፃፍ ይቻላል። አንባቢያንም በበኩላችሁ ብዙ ማከል ትችላላችሁ። ከ፲፱፻፷፮ እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. በነበረው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ በምን ሁኔታ እንደነበረች እና በምን ሁኔታ እንዳለፈች ማተቱ አስፈላጊነቱ አይታየኝም። ***የዚህ ፅሑፍ ዓላማ፣ ገፀ ባህሪያችንን ጠቁሞ፣ ወደ መፍትሔ ለመጓዝ ስለሆነ፣ ዝርዝሩን ከወዲሁ እገታዋለሁ።*** **እናስ አሁን ይኼንን ገፀ ባህሪያችንን የተረዳን የትርምሱ ትውልድ አባላት ምን እናድርግ?**

በመጀመሪያ አሁን ያለንበት ዘመን የትውልድ ኃላፊነቱ የኛ ሳይሆን፤ ከኛ የቀጠለውም ሳይሆን፤ ( **ማለት የውጥንቅጥ ትውልድ - ከ፲፱፻፹፫ እስከ ፳፻ ድረስ** ) ከዚያ ቀጥሎ የመጣው ትውልድ፤ አሁን ያለው ትውልድ፤ ( **የሀገር አድን ትውልድ ከ፳፻ እስከ ፳፻፳ ድረስ** ) መሆኑን ተቀብለን፣ መሪዎችና ዘዋሪ ነጅዎች ሳንሆን ረዳቶች መሆናችንን ማመን። ይህ ቀላል አይደለም። ከትውልድ አንፃር ይህ ዘመን በአሁኑ ሰዓት በዕድሜ በ፳ ዓመት አካባቢ ላሉት ነው። ይህ ትውልድ **የሀገር አድን** ተልዕኮ አለበት። ይኽ መሆኑን አለመቀበል፤ አንድም የራሳችን የትውልድ ዘመን ያልነውን፤ ከ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ያለውን አለመቀበል ነው፤ ወይንም ሽምጥጦ መካድ ነው። አለያ በህይወት እስካለሁ ድረስ ሁሉም የኔነዉ ባይ የታሪክ ስግብግብነት ነው። ወደቁም ነገሩ እንመለስ።

**ዕድሜ ትልቅ ትምህርት ቤት ነው።** እዩሽመገልን ስንሄድ አመለካከታችን በወጣትነት ጊዜ ከነበረን የተለዩ ይሆናል። በማንኛውም የዕድሜ ክልል፤ አንድ ሁኔታ ሲያጋጥም፤ ከፊት ለፊት የታዩዉን መልስ መስጠት አንድ መንገድ ነው። ይኼንን መንገድ የኛው ትውልድ ተክኖታል። ሌላው አማራጭ መንገድ ደግሞ፤ ረጋ ብሎ፤ ላይና ታቹን መርምሮ፤ ግራና ቀኙን አሰባስቦ፤ ሁሉንም አወዳድሮና አጣጥሞ፤ መፍትሄ መሻት ነው። ይኼንን መንገድ ደግሞ የኛው ትውልድ ባሁኑ ሰዓት ሊተገብረው የሚገባው ነው። **ሽምግልና ጊዜ ተፈጅቶ፣ በብዙ ተሞክሮዎች ታልፎ የሚደርሱበት የበሳልነት ወቅት ነው።** "ትደርስበታለህ" ይባል የለ! ይኼም በመሆኑ ሽምግልና ራሱ ሁለተኛውን አማራጭ ይመስላል። "የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" ይባላልና፤ ጊዜ ወስዶ የተገኘ ዕውቀት ጥሩ ምርኩዝ ነው።

ምን ለማድረግ እንፈልጋለን የሚለውን መመለሱ፤ አሁን ቀላል ይሆንልናል። ***ሀገሪቱ ያለችበትን ዕውነታ አጥንቶ፣ የት መሆን ይገባታል የሚለውን ለይቶ፣ ወደዚያ ለመጓዝ የሚያስፈልገውን ሁሉ ማድረግ፤ ይጠበቅብናል።*** ባለንበት የታሪክ ወቅት፤ ዛሬ፤ የሀገሪቱን የፖለቲካ ገሀድ አጢኖ፤ በዚሁ ተመሥርቶ፤ የፖለቲካ ቡድኖችን አመሠራረትና መፈረካከት፤ ጊዜያዊ ትንታኔ መሥጠት ይቻላል። ያለም ነው። ሆኖም ይህ ትልቁንና ሰፊውን ገፅታ ካለመሸፈኑም በላይ፤ በመፍትሄ ፍለጋ ሩጫችን ወቅት ቀበቶ ያስፈታናል። ሽምግልናችን ሊረዳን ይገባዋል። የዚህም መሠረታዊ ምክንያቱ

እኛ የታሪክ ቦታችንን መረዳታችን ነው። ከዚህ ከተነሣን ጉዳዩ፤ ከኛ በላይ፣ ክብደቱ፤ እጅግ የከፋና፣ መፍትሄዉም፤ ያንኑ ያህል ሚዛን ያለው፤ መሆኑን መገንዘባችን ነው። እንደዚህ ሲቀመጥ ደግሞ፤ ለዚህ መፍትሄ ተገዢ ለመሆንና ታሪካዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት የምንሯሯጥና የምንሽቀዳደም ይመስለኛል። የሀገራችንን አጣብቂኝ ሁኔታ፤ ከግለሰብ ማንነታችን በላይ መሆኑን ስንገነዘብና፤ ለዚህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠያቂነታችንን ስንቀበል፤ በአሁኑ ሰዓት እንዳንተባበርና አብረን እንዳንሰራ እንቅፋት የሆኑት ጥቃቅን ልዩነቶች ሁሉ ዋጋ ቢስ ይሆናሉ። ***ተራራ ንደን፣ ጉድጓድ ምሰን፣ ጫካ መንጥረን፣ ያልገቡ ገብተን፣ መለያያ ነጥቦችን ፍለጋ የምናደርገው የኩታራ ጨዋታ ማክተም አለበት።*** መነሻችን የትውልድ ኃላፊነታችንን ለመወጣትና አኩሪ ታሪክ ጥለን ለማለፍ፤ የእዩልኝ ሳይሆን የታሪክ ይፍረደኝ፤ ተግባር መሆን አለበት። ኃላፊነት ከማይሰማቸው ይኼ አይጠበቅም። ወትሮዉንም ሀገሪቱ እዚህ የተዘፈቀችው በነሱው ድጋፍና በሥልጣን ቀነዝናዞች ብርታት ነውና።

እዚህ ላይ፤ አሁንም ለንጉሡ አሽከርነትን የሚሻዉ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ሀገር አዳኝ የሚለው፣ መለስ ዜናውን ሊቅ የሚያደርገው፣ የ“ነፃ አውጭ” መሪዎቹን የሚያመልከው፣ ትግሉን ትዳር ብሎ የያዘው፣ እና ወገኑን እና ሀገሩን በመውደድ ምን ይሻላል ባዩ፤ ባንድነት ከበው ከበሮ ይደልቃሉ የሚል የሕልም ቅዠት ተጠናዉቶኝ አይደለም። የሁኔታውን ክብደት በመረዳት፤ ከግለሰቦችና ከቡድን የበለጠው ጥሪ፤ በያንዳንዳችን አዕምሮ ኢትዮጵያዊነትን ይቀሰቅሳል ከሚል ምኞት እንጅ። የበለጠም የመቀራረብ፣ የመታረቅና፣ የመተባበር፣ ቃና ይስፈንብን።

ስለዚህ፤ <u>የሀገር አድን ትውልድ</u> ተልዕኮ ያለውን፤ የዛሬውን ትውልድ፤ መርዳት አለብን። ከኛ ቀጥሎ የመጣው <u>የውጥንቅጥ ትውልድ</u> ይኼንኑ መከተል ይኖርበታል። በዕርግጥ በኛው ዘመን አተራምሰን ያስረከብው የኢትዮጵያ ሁኔታ በዚህ ትውልድ አመለካከት ላይ ጥሎት ያለፈው ጠባሳ የሚናቅ አይደለም። ይኼንንም ማረም የኛው ትውልድ ተጨማሪ ኃላፊነት አድርገን መውሰድ አለብን። ታዲያ በዚህ ታሪካዊ ተልዕኮን ለመወጣት በምናደርገው መሯሯጥ ብቸኞች አይደለንም። በኛም ትውልድ ሆነ፤ ከኛ በፊት በቀደሙትና በተከተሉት ትውልዶች፤ ችቦ አብርተው ከፊታችን የሚመሩ፤ ብዙ ሀገር ወዳዶች አሉን። እነሱን እንከተል። እኒህ ጀግኖች፤ አጀንዳቸው፤ ራሳቸውን ለመሾም፣ የነሱን ቡድን ለማስቀደም፣ አንዱን የሀገሪቱን ክልል ከሌላው ለመለየት፣ አልነበረም። በነሱ ማለፍ የኛን መሰንበት በመምረጥ እንጅ። ይህ አይደል ሁላችንን የሚያኮራን? ***እንግዲህ መረዳት ያለብን የታሪክ ቦታችን የሚከተበው፤ በድርጊታችን እንጅ፤ በምናስበው፣ በምናወራው፣ በምንፅፈው፣ ወይንም በምንኩራራበት አለመሆኑን ነው።*** ታዲያ እኔም ብሆን የትውልዴን ገፀ ባህሪ አጠናቅቄ ስለምረዳ፤ ትውልዳችን የማይወደውና የማይቀበለውን፤ ይኼ ነውና መፍትሄው፤ ይህንንና ይህንን አድርግ የሚል ቀጭን ትዕዛዝ መስጠቱን አልሞከረውም። ይልቁንም በአፋችን ሁሌ ከማነብነብ የማንቆጠብለትን፤ በተግባር ግን ካጠገቡ ያልተኀራበትነውን መተባበርን ለማስረገጥ ነው። አሁንም የመቀራረብ፣ የመታረቅና፣ የመተባበር፣ ቃና ይስፈንብን። ይኼ “<u>ተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ</u>”፤ ይኼ “<u>ወርቃማ ትውልድ</u>”፤ ይኼ “<u>አብዮተኛ ትውልድ</u>”፤ መተባበር አይችልም፤ የሚለውን አልቀበልም። የታሪክ ድርሻችን ሆኖ፤ የዚህ ትውልድ አባላት፤ በአሁኑ ሰዓት፤ በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥትና በመዋቅሩ፣ በተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖችና ድርጅቶች፣ በባህል፣ በኢኮኖሚና፣ በንግድ ተቋሞች፤ ወሳኝ ቦታዎችንና የመወሰን ሥልጣኑን ጨብጠናል። ታዲያ ይኼንን አጋጣሚ ተጠቅመን፤ ለወደፊቱ ትውልድ አኩሪ ጥላ ጥለን እናልፋለን የሚል ዕምነት አለኝ።